March 20 ቀን 2020 ዓ ም

## ኮሮና ቫይረስን ለመቋቋም መፍትሔዎችን ሁሉ በተግባር እንፈጽም

በመላው ዓለምና በሐገራችንም የተከሰተውን ለሕይወት ጠንቅ የሆነውን ኖቬል የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሽታ ለመቋቋም ከመንግሥት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከጤና ድርጅቶችና ባለሙያዎች፤ ግል ድርጅቶችና ሐገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የጀመሯቸው ሕዝብን ስለበሽታው መንስኤና አመጣጥ የማሳወቅ፤ ራስን ከመንስኤው ስለማግለል፤ ስለመመርመር፤ የሕክምና ዕርዳታ ስለማግኘት፤ እና ከበሽታው አለመያዝ በሃኪም ማረጋገጫ ከተገኘም በኋላ ክትትል ስለማድረግ የማስተማርና የበሽታው ጠንቅ (ቫይረሱ) በሰፊው እንዳይሰራጭ ለመግታት የሚደረገው ጥረት ሁሉ ለሕዝብ ድህነት የሚደረግ የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡

ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች በጣም የበለጸጉ ሐገራት በሀብታቸውና ጠንካራ የጤና ተቋሞቻቸው ብቻ ተማምነው ሳይሆን በቅድሚያ በሳይንሳዊ ተመክሮ ላይ በተመሠረተ የመከላከል ትምህርት ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ በሰፊው ለሕዝብ ማቅረብና ማዳረስ ሲቻል መሆኑ እሙን ነው።

ከወረርሽኙ ለመከላከል ከሚጠቀሱት ዘዴዎች ውስጥ ፊትን አለመነካካት፤ በተቻለ መጠን በመደጋገም እጅን መታጠብ፤ በሽታው የተጠናወተን መሆኑን ካወቅን ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ማራቅ፤ ስለ ሕመሙ ሰፊ ግንዛቤ እንዲገኝ ማድረግ እንዲሁም ሕክምና የሚገኝበትን ሥፍራ ማሳወቅ ይገኙበታል፡፡

ይሁን እንጂ፤ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ተላላፊ የሆነውን ይህን አደገኛ በሽታ ለመከላከልም ሆነ በሽታው ከመዛመት እንዲገታ ለማድረግ እንዲረዱ ከሚሰጡት ትምህርቶች መካከል እጅግ አስፈላጊ የሆነውና በኢትዮጵያዊነት ባህላችን መገለጫ በሆኑት በሕብረሰባዊም ሆነ ባህላዊ ቅርርብ የሚታዩ በእጅ ሠላምታም ይሁን በመሳሳም፤ እንዲሁም ተቀራርቦ በመተቃቀፍ የሚገለጡ የሠላምታ ልውውጦች ምክንያት ሊኖር የሚገባው አካላዊ ርቀት (በእንግሊዝኛው ሶሻል ዲስታንስ) የተዘነጋ ወይም ደብዘዝ ብሎ የቀረበ ይመስላል።

የዓለም የጤና ድርጅት (WHO) ከፍተኛ ባለሙያዎች ወረርሽኙ በሚገኝበት ሐገር ዜጎች በሥራ፣ በምግብ ቤቶች፣ በእምነትና፣ ማህበራዊ ቦታዎች ቢያንስከ ከ2 ሜትር (6 ጫማ ርቀት) በታች መቀራረብ የለባቸውም በማለት አጠናክረው ያሳስባሉ። በባህል ተጽዕኖ ምክንያት ይህን መፈጸም ቢያዳግት ምን ያህል  ከታመመም ሆነ መታመሙ ካልታወቀ ሰው በሰፋት ወዳልታመሙት የማዛመት ዕድሉ የተመቻቸ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ለወገን ደህንነትም ሆነ በበሽታው ጥቃት በተለያየ ደረጃ የሚደርሰውን ቀውስ ለማስወገድ መላ ሊፈለግለት ይገባል እንላለን፡፡

የኢትዮጵያውያን ባህልና የኑሮ ዘይቤ በአካል ቅርርቦሽ ላይ የተገነባ ነው።  ጎን ለጎን ሆኖ ያወጋል፣ይፀልያል፣ ይማራል፣ ይሠራል።  እንደ ምዕራባውያን ተለምዶ የግል (የግሌ) የሚለው ቦታ (ስፔስ) የሚል ነገር አያውቅም።  እንዲያውም እንደዚያ ማሰብ እንደ ነውር ይታያል።  ኮሮና ቫይረስ የሚተላለፈው በእጅ ሰላምታ ንክኪ፣ በመተቃቀፍ፣ በትከሻ ለትከሻ ግላዊና ማህበራዊ መስተጋብር ነው።  የሚመለከተን ሁሉ በማህበራዊ የአካል ቅርርብ የሚገለጹ የሠላምታም ሆነ የደስታ እንዲሁም ሌሎች በመተቃቀፍ የሚገለጹ ባህላዊ መስተጋብሮች በጊዜያዊነት ቢሆን ለማስተው በትኩረት ማስተማር እጅግ ብዙ ሕይወት እንዲተርፍ ይረዳል።  ጉዳዩ ከይሉኝታና ባህል በላይ ነው።  ጊዜ ወሳኝ ነው።  በዘገየን ቁጥር በሽታው ይበልጥ ይዛመታል።

የሕዝባችንን ሕይወት የመታደጉ በጎ ጅምሮች ለመንግሥት ብቻም አይተውም።  ተሰሚነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፤ እድሮችና ማሕበሮች፤ ታዋቂነት ያላቸው ግለሰቦች፤ መንግሥትን እንዲደግፉና እንዲተባበሩ ሁኔታው ያስገድዳል።  የሁሉም ቤተ እምነት መሪዎች በየተቋሞቻቸው ተዋረድ በኩል ምዕመናን ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ማስተማር ስለበሽታው አሳሳቢነትም ሆነ አደገኛነት ግምታቸውን ከፍ በማድረግ ከመርዳቱም በላይ ስለመከላከል

የሚሰጠውን መመሪያ በተግባር በማዋል በኩል ክትትል በማድረግ ተሳትፏቸው ጥሩ ይሆናል። ለእጆቻችን ንጽህናና በመንካት የሚበከሉትን ሁሉ ለማስወገድ ለንጽህናና የየዕለት ሃይጂን ለሚደረገው ጥንቃቄ የመታጠቢያ ውሃና የሳሙና እንዲሁም የጸረ-_ጀርም መከላከያ አልኮሆል_አዘል ፈሳሽ (Sanitizer) በስፋት ለሕዝብ እንዲዳረስ ማድረግ የበሽታውን መዛመት የሚቀንስ በመሆኑ በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅቶች ትብብር የሚደረገው ርብርብ ወሳኝነት አለው፡፡

ጥንቃቄዎቹ "ክፉው ጊዜ እስኪያልፍ" ምዕመናን በቤተ ክርስትያን፣ በመስጊዶች ማህበራዊ ቅርርብ የሚደረጉ ባህላዊ የሠላምታም ሆነ ሌላ ልውውጦች በርቀት እንዲተገብሩ ማስተማር ጠቃሚ ነው።

ከታሪክ እንደምንረዳው፤ በተለያዩ መንስኤዎች በዓለም የተዛመቱ የብዙ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፉ የወረርሽኝ በሽታ ተደጋግሞ ታይቷል። በሐገራችን በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የነበረው ብዙ ሰው የጨረሰው ያሁኑ ዓይነት ተላላፊ በሽታ (የሕዳር በሽታ፣ ስፓኒሽ ኢንፍሉዌንዛ) አንዱ ምሳሌ ነው። ያኔ የነበረው ሣይንሳዊ የዕውቀት ደረጃ እንደዛሬው ያደገ አልነበረም። ያም ሆኖ አባቶቻችንና እናቶቻችን ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር፣ ሰው ለማዳን ጥረዋል። ዛሬም ወገናችን የኮሮና ቫይረስ ሰለባ እንዳይሆን፣ የሀኪሞ ምክሮችን ሙሉ በሙሉ መከተል ነው። ምናልባት ከአብሮነት፣ ባህላዊ ልምድና ከእምነት ጋር የሚጣጣሙ የማይመስሉ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ካሉ፣ እንደበፊቱ በአባቶች ምክር ወደፊት ስለሚፈቱ፤ በማሕበራዊ ቅርርብ የሚተገበሩ የሠላምታ መለዋወጥም ሆነ የሌላ ልውውጦች በርቀት እንዲሆን በስፋት ማስተማር አንዱ ወሳኝ መፍትሔ ነው።

ማሕበራዊ ባህላዊ ሠላምታ በርቀት (ሶሻል ርቀት; ሶሻል ዲስታንስ) የኮሮና ቫይረስ የመከላከያ መፍትሔ ነው!

ማሕበራዊ ሠላምታችንን በርቀት መተግበር አብሮነታችንን አያሳንስም!

ሕይወትን ለማትረፍ ቅድሚያ እንስጥ!

ኢትዮጵያ ለዝላለም ትኑር!

ኢትዮጵያዊነት፡- የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ